# «የኢህአዴግ ፖርላማ የተማሪና የአስተማሪ አይነት ባህሪ ያለው ነው»

የተከበሩ ዶ/ር መረራ ጉዲና

*ዶ/ር መረራ ጉዲና የተወለዱት በአምቦ ወረዳ ቶኬ በሚባል የገጠር አካባቢ ሲሆን የመጀመሪያና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን እዚያው አምቦ ተከታትለው በ1965 ዓ/ም አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ገብተዋል:: ሆኖም በወቅቱ በነበረው የተማሪዎች እንግስቃሴ መኢሶንን በመቀላቀላቸው ለሰባት አመት ያህል እስርቤት አሳልፈዋል::ከእስር ቤት ከወጡም በኃላ በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የጀመሩትን ትምህርት አገባደው የመጀመሪያ ዲግሪአቸውን ያዙ:: ሁለተኛ ዲግሪአቸውን ከግብጽ የዶክትሬት ዲግሪአቸውን ደግሞ ከኔዘርላንድስ አግኝተዋል:: በአሁኑ ወቅት የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባልና በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የፖለቲካል ሳይንስ መምህር የሆኑት ዶ/ር መረራ ጉዲና በወቅታዊ አገራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ከወንድራድ ደብረጽዮን ጋር ሰፊ ውይይት አድርገዋል::*

***ኢትዮጵያ እስከዛሬ ካደረገቻቸው ምርጫዎች አንፃር የ2000 ምርጫ አወዳድረው ቢገልፁልን?***

ከግንቦት 1997 ምርጫ አንፃር ስንመለከተው ብዙ እርምጃዎች ወደ ኃላ ተጉዟል:: በአፄ ኃይለስላሴ ዘመንም ሆነ በደርግ ጊዜ እንዲሁም ኢህአዴግ ብዙውን ጊዜ ካደረጋቸው ምርጫዎች ጋር ሰናነፃፅረው በብዙ መልኩ ተመሳሳይ ነው:: የሰሞኑ ምርጫ ፧ምርጫ ከተባለ የደርግ ዘመንን ምርጫ ይሸታል::

***በአህጉራችን አፍሪካ የሚደረጉ ምርጫዎች ብዙውን ጊዜ ፍፃሜያቸው በደም መፍሰስ እየተጠናቀቁ ይገኛሉ:: /ኢትዮጵያ፣ ኬኒያ፣ ዙምባብዌ.../ እንደ ፖለቲካል ሳይንስ ባለሞያነትዎ ለነዚህ ችግሮች መነሻ ምክንያቶች ምንድነው ብለው ያምናሉ?***

በአጠቃላይ በአፍሪካ ውስጥ ያሉ መሪዎች ወይም ገዢዎች ምርጫ ሲያካሂዱ ምርጫው እራሳቸውን በስልጣን ላይ ለማቆየት እንጂ ተሸንፈው ስልጣንን መልቀቅ አብረው ማሰብ አይፈለጉም:: በአብዛኛው ምርጫዎች በአፍሪካ የሚደረጉት ይቺ ያለንባት አለም ምርጫ ማድረግ ስለምትፈልግ ነው:: በዋነኝነት

ምዕራባዊያን ገንዘብ ለመርዳት እንደ ቅድመ ሁኔታ ምርጫን ስለሚያስቀምጡ የሚደረጉ ምርጫዎች በመሆናቸው ነው፡፡ ወይም በአጭር አማርኛ በነጮች አለም ተቀባይነት ለማግኘት የሚደረጉ ምርጫዎች እንጂ በሃቅ የዲሞክራሲያዊ ስርዓትን በአህጉሪቱ ውስጥ ለማስፈን የሚደረጉ ምርጫዎች አይደሉም፡፡ የህዝብ አመኔታና ከበሬታን አግኝቶ ስልጣን ላይ ለመውጣት፡፡ ያንን ሲያጡ ደግሞ ከስልጣን መውረድ እንዳለባቸው አምነው አይደለም የአፍሪካ መሪዎች እየተንቀሳቀሱ ያሉት ችግሩ እዛ ነው፡፡ ሁኔታው ስለሚፈልግ ብቻ ምርጫ ያከናውናሉ፡፡ ስልጣንን ለመልቀቅ ዝግጁ ስላልሆኑ አንድ ሺ አንድ ምክንያቶችን ፈጥረው ስልጣን ላይ ለመቆየት ይቀሰቅሳሉ፡፡

በዚህም ምክንያት የሚፈጠሩ ቀውሶች ደግሞ ከፍተኛ ደረጃ ላይ ይደርሳል፡፡ መብቱን የተነጠቀው እና በመብት ነጣቂው መሃል በሚደረገው ግጭት የብዙ ዜጐች ህይወት አደጋ ላይ ይወድቃል፡፡ የአፍሪካ መሪዎች ዋነኛ ችግር ይህ ነው፡፡

***በርስዎ ግምት ከዚህ በኃላ የሚደረጉ ምርጫዎች ዕጣ ፈንታቸው ምን ይሆናል?***

በአብዛኛው ነገሮችን ስናስተውላቸውና በዚህ ምርጫም እንደተረዳነው ኢህአዴግ የምርጫ ጥያቄ አካባቢ ጉዞውን የጨረሰ ይመስላል፡፡ ነፃና ፍትሐዊ ምርጫ ለማድረግ እንደማይችል ከግንቦቱ ምርጫ የተረዳ ይመስላል፡፡ በኢትዮጵያ ህዝብ አመኔታ እና ከበሬታ በነፃና ፍትሀዊ ምርጫ፣ በህዝብ ድምፅ ስልጣን ላይ መቆየት እንደማይችል ኢህአዴግ የተረዳ ይመስላል፡፡ ከዚህ በኃላም የኢትዮጵያ ህዝብ፣ የአገሪቱ ዲሞክራሲ ሃይሎች ኢህአዴግ ነፃና ፍትሃዊ ምርጫ እንዲቀበል የጨዋታውን ሜዳ እንዲያስተካክል መደራደርና ማስገደድ እስካልቻልን ድረስ በኢህአዴግ ስር የሚደረጉ ምርጫዎች ነፃና ፍትሃዊ የሚደረገው ሙከራ ያበቃለት ይመስላል፡፡

***ጠቅላይ ሚኒስተር መለስ ዜናዊ ከሁለት ዓመት በኃላ «ስልጣን እለቃለሁ» ብለዋል፡፡ የሳቸው ከስልጣን መልቀቅን ተከትሎ ምን ይከሰታል ብለው ያስባሉ?***

በመጀመሪያ ደረጃ ጠቅላይ ሚኒስተሩ ስልጣናቸውን እንደሚለቁ እርግጠኛ አይደለሁም፡፡ ምክንያቱም በሚሰጧቸው የእንግሊዘኛ ቃለ ምልልሶች «ልለቅ እችላለሁ» የሚል አለ፡፡ «እችላለሁ» ማለት እለቃለሁ ማለት አይደለም፡፡ በሌላ ጊዜ ደግሞ «ፓርቲዬ ከፈለገ ወይም ካመነበት» የሚል ነገር ይጨመርበታል፡፡ ይህ ደግሞ የሳቸውን ስልጣን መልቀቅ እርግጠኛ ለመሆን አይቻልም፡፡ «ከዚህ

በኃላ አልወዳደርም ስልጣኔንም እለቃለሁ» ብለው አፍ ሞልተው የተናገሩበት ሁኔታ አላጋጠመኝም:: ስለዚህ የእርሳቸው መልቀቅ በጣም እጠራጠረዋለሁ::

*«ተቃዋሚዎች በኢትዮጵያ ፖለቲካ ውስጥ እንቅስቃሴአቸው እየተዳከመ ነው» የሚል ትችት ይሰነዘራል:: ምንድነው የእርስዎ ምላሽ?*

እርግጥ የተቃዋሚዎች እንቅስቃሴ የተጠበቀውን ያህል ለውጥ እያመጣ አይደለም:: የተጠበቀውን ያህል ልዩነታቸውን አቻችለው በመሰረታዊ የአገሪቱ ጉዳዬች ላይ መተባበር አልቻሉም:: ይህ በግልፅ ይታያል:: ለዚህ ችግር መከሰት በእኔ እምነት ምክንያቱ ከሁለት አካባቢዎች የመነጩ ናቸው:: አንደኛው ገዢው ፖርቲ ጠብመንጃውን ይዞ በጉልበት ይንቀሳቀሳል:: የአገሪቱንም ሀብት ሙሉ በሙሉ ተቆጣጥሮ ተቃዋሚዎችን ለመከፋፈል ይንቀሳቀሳል:: ስልጣኑም በእጁ ስላለ በስልጣኑ ተጠቅሞ ያሻውን ተግባር ይፈጽማል:: ስለዚህ ገዢው ፖርቲ ጠንካራ እና እራሳቸውን የቻሉ የተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶች በኢትዮጵያ ምድር እንዲኖሩ ሁኔታዎችን ያለማመቻቸት ብቻ ሳይሆን ጨርሶ እንዳይኖሩ ከላይ እንዳልኩት ባለው ሃይል ሁሉ ይንቀሳቀሳል:: በተቃዋሚዎች በኩል የገዢውን ፓርቲ የሃይል ጫናዎች (ስልጣንን፣ ጠብመንጃን፣ ገንዘብን ይዞ የሚንቀሳቀሰውን ፖርቲ) መቋቋም አስቸጋሪ ሆኗል:: በተቃዋሚዎች ላይ ሌላ የተቃዋሚዎች ተቃዋሚ በመፍጠር ትግሉን አዳክመውታል ብቻ ሳይሆን እንከን በእንከን እንዲሆን እየተደረገ ነው:: ቁጥራቸው ቀላል የማይባሉ የፖለቲካ ድርጅቶች የተመሰረቱት ኢህአዴግን ለመቃወም ሳይሆን ተቃዋሚዎችን ለመቃወም የተቋቋሙ የፖለቲካ ድርጅቶች ብዙ አሉ:: ሚናቸው በአገሪቷ ውስጥ ዲሞክራሲያዊ ስርአትን የመፍጠር ወይም እራሳቸውንም ተወዳዳሪ አድርገው ለመመረጥ ፍላጎት ኖሯቸው ሳይሆን ወይም ፖለቲካዊ እንቅስቃሴ ኖሯቸው የህዝብን አመኔታና መከበርን ለማግኘት ሳይሆን ተቃዋሚዎችን ለመቃወም ኢህአዴግ ያደራጃቸው ብዙ የፖለቲካ ድርጅቶች አሉ::

ያንን ሁሉ ተቋቁሞ በዚች ደሃ አገር ተቃዋሚዎች የሚጠበቅባቸውን ማድረግ አልቻሉም:: ከገዢው ፖርቲ የሚደርስባቸውን ጫና ተቋቁመው የሚጠበቅባቸውን ለማድረግ አልቻሉም:: ነፃ ናቸው እራሳቸውን ችለው ይንቀሳቀሳሉ የሚባሉ የፖለቲካ ድርጅቶች /ቅንጅትን መጥቀስ ይቻላል/ የሆነውን ነገር የምናውቀው ጉዳይ ነው:: ከግንቦቱ ምርጫ በኃላ የተሻለ ውጤት ካስመዘገቡት ፖርቲዎች መካከል አንዱ የኛ ድርጅት ነው:: ከዚህ ቅፅበት በኃላ ድርጅታችን ላይ ኢህአዴግ እስካሁን ያላባራ ጦርነት አውጆበት እየተንቀሳቀሰ ነው:: አባሎቻችን በአዲስ አበባም ሆነ በሌሎች ቦታዎች በሚታደል መሬት እየተገዙ በጠራራ ፀሃይ በገዢው ፖርቲ ሲገዙ፣ ሲደለሉ፣ ሲያስኮበልላቸው

ኢህአዴግን እናገኘዋለን:: ባለፈው ጊዜ ጠቅላይ ሚኒስተሩ /የኑሮ ውድነትን አስመልክተው ሪፖርቲ ሲያቀርቡ/ በሚገባቸው ቋንቋ ጠይቄ ነበር:: ለመመለስ አልፈለጉም Commercialization of Politic በተለይ /ፖለቲካን ወደ ንግድነት/ የመቀየር ሁኔታ በስፋት በአሁኑ ሰአት ይታያል:: በዚች ደሀ አገር ይህንን መቋቋሙ ቀላል አልሆነም::

ሁለተኛው ችግር እራሳቸው ተቃዋሚ ፖርቲዎች ናቸው:: የተቃዋሚ ፖርቲ መሪዎች የራሳቸው ጠባብ ዕይታ (ምናልባትም አንዳንዶቹ በራሳቸው ህልም ውስጥ መዋዠቁ) ተቻችሎ ከመስራት ይልቅ ትናንሽ ፖርቲዎችም ቢሆን እንኳን የዛ መሪ መሆን እንጂ ትልቅ ፖርቲ ውስጥ ያላቸውን ድርሻን እንደ መልካም ሁኔታ አለመቁጠራቸው:: አንዱ ችግር ነው የቁርጥራጭ ፖርቲ አመራር መሆንን ይመርጣሉ:: ከዚህ ከፊውዳል ኢትዮጵያ የወረስነው አንዳንድ ፀባዬች ተቃዋሚዎች አካባቢ ይታያል:: ገዢው ፖርቲ ከሚፈጥረው ችግር ብቻ ሳይሆን እራሳቸው ተቃዋሚዎች ጫና ተቋቁመው ልዩነታቸውን አቻችለው በሰጥቶ መቀበል ፖሊሲ ላይ ችግሮቻቸውን ፈተው ከሌሎች ጋር የመስራት ሃገራዊ ጉዳዬች ላይ መስራት የሚጠበቅባቸውን ያክል መስራት አልቻሉም::

ከዚህ መደምደም የሚቻለው ለተቃዋሚዎች እንቅስቃሴ በታሰበው ፍጥነት ያለመጓዝ ዋነኛው ምክንያት በሁለት ከፍለን ማየት ይቻላል:: የመጀመሪያው ገዢው ፖርቲ የሚያደርስባቸው ጫና በዚች ደሀ ሃገር ቀላል ያልሆነ ፈተና ነው::

ሌላው ደግሞ በራሳቸው በተቃዋሚዎች ዙሪያ ያለ ችግር ነው:: ካልለቀቀን የፊውዳል አስተሳሰብ ሊሆን ይችላል:: ሰጥቶ የመቀበል መርሆችን የተከተለ አስተሳሰብ በተቃዋሚዎች ውስጥም አልሰረፀም:: እንዲህ አይነት ትውልድ አገሪቷ እስከአሁን አላፈራችም:: የነበረው የአዒያዊ አስተዳደር እና የፖለቲካ ባህል አለ:: በመቀጠል ደግሞ የአፈና ስርአት ጉልቶ የታየበት ሁኔታ ቆይተናል:: አሁንም ከእንዲህ አይነቱ ችግር ለመላቀቅ ቀላል አልሆነም::

ተቃዋሚዎች በጋራም ሆነ በየግላቸው አገራዊ በሆኑ ጉዳዬች ዙሪያ መተማመን፣ መረዳዳት፣ መወያየት፣ ችግሮችን በጋራ የመፍታት ባህልን የማዳበር ሁኔታዎች መስፈን ይኖርባቸዋል:: ልዩነቶች እንዳሉን ሁሉ አብረን መስራት ይጠበቅብናል:: ይህ ባለሆነበት ሁኔታ ግን የተሳካ የዴሞክራሲ ስርዓት ግንባታን ለማስፈን አስቸጋሪ ነው የሚሆነው::

***የተቃዋሚ ፖርቲዎች ሲመሰረቱ አባላት ስብሰባ ላይ ብዙም አይጠነቀቁም:: በዚህም ምክንያት በተደጋጋሚ ለፖለቲካው ትግል ወጤታማነት***

*የሚጥሩ ሳይሆን ለግላዊ ጥቅማቸው ተገዢ የሆኑ አባላቶችን ያበዛሉ:: እየተባለ ትታማላችሁ በዚህ ዙሪያ የሚሉኝ?*

ጥንቃቄ የሚባለው ጉዳይ በጣም አስቸጋሪ ነው:: ምክንያቱም መቼም ሰዎችን ለፖለቲካ ትግል ስትመለምል በተወሰነ ደረጃ ወይ የሚመለምለው ሰው ፍላጐት አለ:: (መታገል እፈልጋለሁ ብሎ ይመጣል) አልያም የኛ ካድሬዎች ከኛ ጋር ታገል ብለው ይጋብዙታል:: በሁለቱም መንገድ ሰውን መዝኖ የማወቁ ሁኔታ ሜዲካል ሳይንስም ቢሆን እንኳን ቢሆን እስካሁን አልደረሰበትም:: ምን ያስባል፣ ህልሙ ምንድነው፣ የተጠጋው ለምንድነው፣ የዛሬ 20 አመት ከእኔ ጋር አብሮ ይቆያል ወይ? የሚለውን ለመመለስ በሰለጠኑት አገራት እንኳን ከሜዲካል ዕውቀት በላይ ስለሆነ የሚቻል አይሆንም:: አንድ የማይካድ ችግር አለ:: በዚች ደሃ ሀገር ድህነት እያስከተለ ያለው የፖለቲካ ትግል ወጥነት እንዳይኖረው አድርጓል::

እራሱን ችሏል:: በልቶ ያድራል የምትለው በተለይ ሙሁሩ አካል የፖለቲካ ትግል ውስጥ አይገባም:: በተለይ ደርግ የፈጠረው ተፅእኖ ምክንያት ኤሌክትሪክ እና ፖለቲካን በሩቁ እንዲል አስገድዶታል:: የተጨቆነ ነው የመታገል ፍላጐት አለው ተብሎ ፖርቲን የተቀላቀለው ደግሞ የተሻለ እንጀራ ሲያገኝ ምን ጊዜ እንደሚከዳህ አይታወቅም:: በተለይ አንዳንዳቼማ እጅግ አስገራሚ በሆነ ፍጥነት ሲከዱ ታያለህ:: በእኛ ድርጅት ረጅም ጊዜ የቀለብናቸው ድርጅቶች፣ ያሳደግናቸው ልጆች የተሻለ እንጀራ ሲያገኙ የከዱበት ሁኔታ በጣም ያስገርመኛል:: ከኛ ጋር እየበሉ እየጠጡ ከኖሩ በኃላ ባልተጠበቀ ሁኔታ ደህና ሁኑ እንኳን ሳይሉ የሆድ ነገር ሆኖባቸው ነው:: ለተሻለ አላማ ለመታገል እንዳልሄዱ የታወቀ ነው:: ይህ ምንድነው የሚያሳየው በልቶ የሚያድረው «ይቺን አታሳጣኝ» ብሎ በፍርሃት ቆፈን በስፋት ተጠምዶ ነው ያለው:: ለምሳሌ ከኃላችን ሆነው በርቱ የሚሉን እውቀቱም ያላቸው፣ ማደራጀትም የሚችሉ ሰዎች በርቱ እንጂ ሲያደራጁ አታያቸውም:: ልጄ፣ ሚስቴን፣ እያሉ በስጋት ምክንያት የፖለቲካን ሪንግ አይደፍሩም:: ይህ ደግሞ ከምንም የመነጨ አይደለም:: የአማራጭ ጉዳይ ነው:: የምበላውን አላጣም ብሎ ሰው በሙሉ ልቡ የሚንቀሳቀስበት ሁኔታ አልተመቻቸም::

የሌላው ደግሞ በፖለቲካ ስም በልቶ ጠግቦ ለመኖር ሊሆን ይችላል:: እኛ ከምንሰጠው ፍርፋሪ እና ትንንሽ ነገሮች የተሻለ እንጀራ ሲያገኝ ከላይ እንደገለፅኩት ደህና ሁኑ ሳይል የበላበትን ውጭት እረግጦ በብርሃን ፍጥነት ከድቶህ ሲሄድ ይስተዋላል::

ጥንቃቄ በሚለው እረገድ ቀላል የማይባል ፈተና ነው ያለው፡፡ ብዙዎች ይህንን ሲሉ እንደቀላል ነው የሚያዩት፡፡ ይህንን ለማድረግም የአገሪቱ የኢኮኖሚ ሁኔታም የፖለቲካውን ፈተናውን እጥፍ ድርብ አድርጐታል፡፡

አንድ በጣም የሚያስቀኝ ነገር አለ፡፡ ኢህአዴግ ግምገማ ይላል፡፡ የኢህአዴግ ግምገማ የሚያመጣው ነገር ቢኖር የፖለቲካ ታማኝነትን አጉልቶ እንዲወጣ የሚያደርግ እንጂ ነገሮችን ከልብ ለውጥ እንዲመዘገብባቸው እያደረጉ አይደለም፡፡ ሙስናን ብንመለከት እኛ በሌብነት ይዘን ያባረርናቸው ኢህአዴግን ሲጠጉ፣ ሲሾሙ ታያለህ፡፡ ስለዚህ ከሃገሪቱ አጠቃላይ የኢኮኖሚ እና የፖለቲካ ሁኔታ የሚመጡ ችግሮች አሉ፡፡ እንደሚባለው እከሌ በሃቅ ለፖለቲካዊ ትግል ይሰለፋል፣ ለአላማው ይሞታል ብሎ ለይቶ ለመመልመል ዘርፈ ብዙ ችግሮች አሉብን፡፡ መጀመሪያ እነዚህ ችግሮች መፈታት አለበት፡፡

## *ይህ ሁኔታ የህዝቡን ፖለቲካዊ የትግል እንቅስቃሴ ይገታዋል?*

ይገታዋል በሚለው ላይ አልስማማም፡፡ ነገር ግን ይጐዳዋል፡፡ ህዝቡ መብቱ እስከተነካ፣ ችግሮች እስካሉ ድረስ፣ ክብሩ፣ ነፃነቱ እስካልተተገበሩ ድረስ ትግል ማድረጉ የማይቀር ነው፡፡ ዳቦ ያጣ ህዝብ ሲርበው መታገሉ አይቀርም፡፡ ለወደፊት ለልጆቹ ጥሩ ነገር የማይፈጥር ከሆነ ህዝቡ መታገሉን አያቆምም፡፡ መታገል እንኳን ባይችል መሰደድን መምረጡ አይቀሬ ነው፡፡ በሰሜን አሜሪካ፣ በአውሮፖ የሚታየውም የኢትዮጵያዊያን ቁጥር መብዛት የሚጠቁመው ይህንኑ ነው፡፡ አይናቸውን ጨፍነው የመጣው ይምጣ ብለው በየአቅጣጫው የሚሰደዱ ኢትዮጵያዊያን ቁጥር መጨመር የሚያሳየው ይህንን ነው፡፡ መታገል ባለመቻላቸው ስደትን የመረጡ ናቸው፡፡ አሁን ጥያቄው ማን ይታገል ነው፡፡ አንዱ ጡረታ ሲወጣ ሌላው ይተካል፡፡ እርግጥ ትግል ይጎዳል ትግሉ ግን ይቀጥላል፡፡ የእኛ ብቻ ሳይሆን የአለም ታሪክ በዚህ ሁኔታ የተሞላው ችግሮች እስኪፈቱ የሰው ልጅ የሚፈልገውን እስኪያገኝ ድረስ የተሻለ ህይወት እና ኑሮ እስኪያገኝ ድረስ ለመብቱ፣ ለክብሩ ለነፃነቱ ይታገላል፡፡ ስለዚህ ይገታል የሚለው አስቸጋሪ ነው፡፡ ሊጎዳ ግን ይችላል፡፡ የመፍትሄ ዘመኑ የተሻለ ሁኔታ የመፍጠሩ ሊረዝም ይችላል፡፡ ለምሳሌ የእኛ ትውልድ ላለፉት 35-40 ዓመታት ታግሏል፡፡ ከተማሪ ንቅናቄ (ከነመንግስቱ ነዋይ) ጀምሮ ሰፊ የሆነ ህዝባዊ ትግል በተለያየ ደረጃ ይካሄድ ነበር፡፡ አሁንም እየተካሄደ ነው፡፡ ስለዚህ ትግሉ ሙሉ ለሙሉ የተዳፈነበት ሁኔታ የለም፡፡ ወደ ኃላ የሚሄድበት ሁኔታዎች ይኖራሉ፡፡ ሙሉ ለሙሉ የተዳፈነበት (የሚጠፋበት) ሁኔታ ግን የለም፡፡

*ፓርላማ በመግባታችሁ ካልገቡት የተሻለ ምንም አይነት የዲሞክራሲያዊ ግንባታ አስተዋፅኦ የላችሁም:: እንዲያውም «የራሳችሁን እንኳን የህዝብ አንደራሴ ከመሆናችሁ አንፃር የመናገር መብት ማስከበር አልቻላችሁም» ለሚለው ወቀሳ ምን ምላሽ ይሰጣሉ?*

በአጠቃላይ በኢትዮጵያ የፖለቲካ ሁኔታ ውስጥ ፓርላማም የገባውም ሆነ ያልገባውም በመሰለው መልኩ ለመታገል ነው:: ያዋጣል፣ የተሻለ ውጤት ያዋጣል በሚለው መንገድ የመታገል ሁኔታ ነው:: ፓርላማ የመግባትም ያለመግባትም የአለም መጨረሻ አይደለም:: ፓርላማም ገብተው በሃቅ ትግሉን የቀጠሉ አሉ:: የሚል ግምት አለኝ:: ፓርላማም ሳይገቡም በሃቅ ህዝባዊ ትግሉን የቀጠሉ ያሉ ይመስለኛል:: ስለዚህ ፓርላማ የመግባት ያለመግባት በጠቃላይ በአገሪቷ የፖለቲካ ትግል ላይ በሃቅ የመታገል እና ያለመታገል ጥያቄ እንጂ የመግባባት እና ያለመግባባት ሁኔታ ያን ያህል ክብደት የሚሰጠው ጉዳይ አድርጌ አልወስደውም:: የዛን ጊዜም ቢሆን ፓርላማ ገብቶ ትግሉን መቀጠል ነው የሚሻለው ወይስ ከዛ በላይ ገፍቶ የመታሰሩን አማራጭ መያዝ ነው የሚሻለው የሚለውም ጥያቄ ነበር:: በእኔ እምነት የትም ሆንክ ትግሉን የመቀጠል ሁኔታ ተደራጅቶ በሃቀኝነት የህዝብ ጥያቄዎችን አንግቦ የመንቀሳቀሱ ሁኔታ ነው እንጂ የመግባት እና ያለመግባቱ የአለም መጨረሻ ሆኖ አላየውም::

ፓርላማን የመረጡ የሚችሉትን ያህል እየሞከሩ ይመስለኛል:: ላለፉት 2 እና 3 ዓመታት የምንችለውን ያህል ባለው የኢትዮጵያ ሁኔታ የሞከርን ይመስለኛል:: ፓርላማ ያልገቡትም በራሳቸው መንገድ ለትግሉ አስተዋፅኦ ለማድረግ የሚችሉትን አስተዋፅኦ ያደረጉ ይመስለኛል:: ዞሮ ዞሮ ውጤቱ ምንድነው? የሚለውን የታሪክ ሚዛን ወደፊት የሚፈታው በመሆኑ ለታሪክ ተመራማሪዎች መተው የተሻለ ይመስለኛል:: ነገር ግን በአጠቃላይ ሁኔታው ዋናው ሚዛን ትግሉ የመቀጠል እና ያለመቀጠሉ በሃቅ መታገሉ እና ያለመታገሉ ሁኔታ ነው የገቡትም ሆነ ያልገቡትም ከዚህ አንፃር ነው መለካት ያለባቸው ሁለቱም ወገኖች ግን አቅማቸው የፈቀደውን ሞክረዋል::

*ፓርላማ ውስጥ የራሳችሁን የመናገር መብት ማስከበር ሳትችሉ እንዴት የወከላችሁን ህዝብ ድምፅ ለፓርላማ ማስደመጥ ትችላላችሁ?*

ፓርላማ ስንገባ ፓርላማ ብቻውን የነፃነት ደሴት ይሆናል:: ብቻውን ዲሞክራሲያዊ ስርአት የሚንፀባረቅበት ይሆናል:: ብለን አይደለም:: ያደራጀናቸው የሰው ሃይል፣ የምናንቀሳቅሰው መዋቅር እና የፖለቲካ ትግላችንን ለማድረግ ውስጥ ሆነን ነው? ወይስ ከፓርላማ ውጭ ሆነን የሚለው ከአጠቃላይ ችግሮች

አንፃር የትኛው መንገድ ይሻላል? በሚለው እንጂ በፓርላማ አካባቢ ደቂቃ እየመዘነ እንድትናገር እየተደረገ:: ለውጥ ይመጣል ብለን አይደለም:: ፓርላማ ብቸኛው ደሴት ነው:: ለማለትም አይደለም:: ፓርላማ አጠቃላይ የኢትዮጵያ ፖለቲካ ነፀብራቅ ነው:: ፓርላማ ውስጥ ጥሩ ዲሞክርሲያዊ ስርአት ይኖራል ብሎ ከፓርላማ ውጭ ስትወጣ አምባገነን መንግስት ነው ልንል አንችልም:: የኢትዮጵያ መንግስት የኢትዮጵያ መንግስት ነው:: ተፈጥሮው አንድ ነው ፓርላማ በመግባታችን አባላታችን ትንሽ ተንቀሳቅሰው የመስራቱ ሁኔታ እንዲመቻች አንዳንድ የተገነቡ መዋቅሮች እንዳይፈርስ ህልውናን የመጠበቅ ስራ እንድንሰራ እና ኖረን ትግሉን የመቀጠል ሁኔታ ለመፍጠር በሚለው አቅጣጫ ሊጠቅም ይችላል:: ከዛ ውጭ ግን ፓርላማው የነፃነት ደሴት ሆኖልን እንደፈለግነው ለመንቀሳቀስ አላስቻለንም:: አባላቶቻችን ወደ መረጣቸው ህዝብ ተጉዘው ለማነጋገር ያልቻሉበት ሁኔታ አጋጥሞናል::

ባሳለፍነው ምርጫ አባላቶቻችን በመደብደባቸው ነው ከምርጫው እራሳችንን ያገለልነው:: ያለውን አጠቃላይ ግፊት ፈርተው ከአገርም የጠፉ የፓርላማ አባላቶችም አሉ:: ፓርላማ ውስጥ ተመችቶን ነው ያለነው የሚል ግምት የለንም::

***ብዙ ጊዜ ፓርላማ ውስጥ አናዮትም?***

ምክንያቱ ቀደም ብዬ የገለፅኩት ነው:: ፓርላማ ሶስት ነገሮች ይጠበቁበታል:: ጠንካራ ፓርላማ ከሆነ አንደኛው ስሪ አስፈፃሚውን የሚቆጣጠር ፓርላማ ነው:: ሌላው የጠንካራ ፓርላማ መገለጫው ጥሩ ህጎችን ማውጣት ነው:: ስራ አስፈፃሚውን መቆጣጠር ቢያቅተው ጥሩ ህጎችን ያወጣል::

ቢያንስ አሁን ባይተረጉሙ ከጊዜ በኃላ ተግባራዊ ሊሆኑ የሚችሉ ህጐች ሊኖሩ ፓርላማው ምክንያት ሊሆን ይችላል::

ደካማ የሚባለው ፓርላማ ደግሞ በያንስ በፈረንጅኛው (Talking shop) የመነጋገሪያ መድረክ ወይም የመጯጯሂያ መድረክ መሆን መቻል አለበት:: ሌላው አንኳን ባይሆን ተጯጩሆ፣ የህዝብ ችግሮችን አንስቶ ተነጋሮ መለያየት አንድ ነገር ነው ስራ አስፈፃሚውን መቆጣጠር ካልተቻለ፣ ጥሩ ህግ ማውጣት ከተሳነን ቢያንስ የመጯጯኸያ መድረክ መሆን መቻል ነበረበት:: ነገር ግን የኛ አገር ፓርላማ ከ Talking shop በታችም ጭምር ነው:: ለመጯጯህ እንኳን እድል አይሰጥም:: 3፣ 4፣ 5፣ ደቂቃ እየተባለ ምን አጠናችሁ ይህንን ጥሩ ሰራችሁ ተባብለን ከስራ አስፈፃሚው ጋር ለመጯጯህ አድል አልሰጠንም::

የመጨረሻውን የፓርላማን ሚናን እንኳን ማሟላት ያልቻለ ፓርላማ ነው:: በዚህ ሁኔታ ደግሞ የሕዝቡን ብሶት እንኳን ለመናገር የሚያስችል ሁኔታ

በሌለበት ሁኔታ ጊዜ መግደሉ ተገቢ አይደለም፡፡ የፖርላማ አባል የሆንኩት የመረጡኝ ህዝብ ብሶት ለመግለፅ እንጂ ዋና ስራዬ በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ስለሆነ ለመናገር በማይቻልበት ሁኔታ ሄጄ ፖርላማ ጊዜ ከመግደል በዩኒቨርስቲ ውስጥ ስራዬን ብሰራ ተመራጭ ነው በሚል ነው፡፡ ትልልቅ ስራዎች እያሉህ ፖርላማ ሄዶ ዝም ብሎ መቀመጡ አስፈላጊነቱ ስላልታየኝ ነው፡፡

*ጠ/ሚኒስትሩ የኑሮ ውድነትን አስመልክተው ሪፖርት በሚያቀርቡበት ወቅት «የሚበላውን ያጣ ህዝብ መሪውን ይባላል» ብለው ሲናገሩ በክብርት ምክትል አፈ ጉባኤዋ ንግግርዎት እንዲቆም ተደርጓል ቀጥሎ ሲናገሩ የነበረውን ለአንባቢያን ሊገልጹልን ይችላሉ?*

ሁለተኛው ዙር እድል ቢሰጡኝ ኖሮ ብዙ ነጥቦችን ማንሳት እፈለግ ነበር፡፡ ፖርላማ ማለት ለክርክር ክፍት የሆነ አገራዊ መድረክ ነው፡፡ የኢህአዴግ ፖርላማ ግን የተማሪና የአስተማሪ አይነት ባህሪ ያለው ነው፡፡ ጥያቄ ይጠይቃሉ ፤ሌክቸር ይሰጣሉ፤ ከዛ በኃላ ሌክቸሩን አዳምጠህ በዛው ትወጣለህ፡፡ ለምሳሌ በዛን እለት ሲከነክነኝ የነበረው እና እድል ቢሰጡኝ መናገር እፈልግ የነበረው ጠቅላይ ሚኒስተሩ ደጋግመው ከኢትዮጵያ ህዝብ 85 በመቶ ገበሬ ነው፡፡ በኑሮ ውድነቱ ገበሬው አልተጎዳም ሲሉ ተደምጠዋል፡፡ እኔ የገበሬ ልጅ ነኝ እንዲሁ በተለያየ ጊዜ ወደ ገጠሪቱ ኢትዮጵያ ስንቀሳቀስ አያለሁ፡፡ ገበሬ አባሎቻችንም እኛ ዘንድ ሲመጡ አያለሁ እህት፣ ወንድም፣ ቤተሰቦቼ፣ ዘመዶቼ በማዳበሪያ ዕዳ ለልጆች ማዳበሪያ መግዢያ ለብዙ ነገሮች እርዳን ብለው ሲመጡ ታያለህ፡፡ ከማንም በላይ በዚህ የኑሮ ውድነት እየተጎዳ ያለው የኢትዮጵያ ገበሬ ነው፡፡ ገበሬው የሚያመርተው በአመት አንድ ጊዜ ብቻ ነው፡፡ ከዛች ካገኛት ውስን ገንዘብ በቀን በቀን ነው የሚያመጣው፡፡ ምርቱ በአመት አንዴ ሆና ሳለ ወጪው ግን በቀን ነው ይህ አካሄድ ባልተቀየረበት ሁኔታ የኑሮ ወድነቱ ገበሬው ላይ አልታየም ማለት የሚያስተዛዝብ ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ መንግስት ያመጣው የማዳበሪያ ዕዳ አለ፡፡ ይህንን ደግሞ በየትኛውም ጥናት ማረጋገጥ ይቻላል፡፡ ገበሬው በአንድ ኩንታል ጤፍ 500 በር ስላገኘ አይደለም፡፡ ይችን 500 መቶ ብር አመቱን ሙሉ ነው የሚመነዝሩት፡፡ በዚህ ሁኔታ ያለን ገበሬ «ኑሮ ተመችቶታል» ማለት የሚዋጥ ነገር አይደለም፡፡ የጠቅላይ ሚኒስትሩ ችግር የእይታ ይመስለኛል፡፡ ሚኒሊክ ቤተመንግስት ተሆኖ ኢትዮጵያን መመልከትና ከዛ ውጭ ሆኖ ኢትዮጵያን መመልከት በጣም ይለያያል፡፡

ለማኙ በየቦታው ሲያስቸግር የሚበሉት ያጡ ህፃናት ዳቦ ዳቦ እያሉ እራሳቸውን ለመኪና አደጋ አጋልጠው መኪና መሀል ሲተራመሱ ጠ/ሚንስትሩ ላያጋጥማቸው ይችላል:: ምናልባት ደህንነታቸውን ካልነገርናቸው በስተቀር ችግሮችን ለማወቅ ይቸገራሉ:: የሳቸው ችግር የእይታ ነው:: ህዝብ ውስጥ የሚኖር እየኖርን የምናየው የታረዙ ሰዎች እና ቀደም ሲል የተሻለ ሰው ነው ብለን የምንገምተው ሰው ዛሬ እራበኝ ብሎ የዳቦ ጥያቄ ሲያቀርብልህ የኑሮ ውድነቱ ገበሬውን አይመለከትም ማለታቸው ከየት የመጣ ነው ብዬ የመጠየቅ ፍላጎት ነበረኝ:: እግረ መንገዴን ያንን የተሳሳተ ሪፖርታቸውን ደጋግመው እንዲያጤኑት ለመምከር ፈልጌ ነበር:: ነገር ግን አልተሳካም::

ሌላው ደግሞ ጠቅላይ ሚኒስተሩ ያነሷቸው ነጥቦች ላይ ለምሳሌ የጦርነቱ ሁኔታ አስመልክቶ መናገር እፈልግ ነበር:: እንደሚታወቀው የሶማሊያ ጦርነት ኢኮኖሚያችንን እየበላ ነው:: የህይወት ዋጋ ብቻም አይደለም:: ቀላል ባልሆነ መንገድ በሺህ የሚቆጠር ሰራዊት አንቀሳቅሰን ሰው ሀገር ስንሰድ ከሚበላው ምግብ ጀምሮ ታንኩ የሚንቀሳቀስበት ነዳጅ ወዘተ ብዙ ሚሊዬን ነው ይፈጃል:: ለሽርሽር የተኬደበት ሁኔታ አይደለም:: ያ ወጪ በሀገሪቷ ላይ ቀላል ያልሆነ ተፅእኖ አለው:: በዚህ ጦርነትም ምን ያህል ወጪ እንደወጣ ጊዜው ከአመት በላይ ወስዷል:: ምን ያህል ቢሊዬን ወይም ሚሊዬን በዚህ ጦርነት ወጪ እንደተደረገ ለኢትዮጵያ ህዝብ አልተገለፀም::

በኤራትራም በኩል ቢሆን «ጦርነት የለም ሰላምም የለም» የሚባለውን ሁኔታ ነው የሚያሳየው:: ላለፉት አስር አመታት በመቶ ሺዎች የሚቆጠር የጦር ሃይል ድንበር ላይ ተቀምጧል:: ይህ ጦር ከቀለብ ጀምሮ የተለያዩ ወጪዎች ያስፈልጉታል:: ስለዚህ የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ጦርነት ላይ ነው:: ይህ ደግሞ ለኢትዮጵያ ህዝብ በግልፅ ሊነገረው ይገባል:: ይህ በፖርላማው ተነስቶ መጯጯህ ይቻል ነበር::

ዳታን አስመልክቶ የአሰባሰብ ሁኔታው ብዙ አጠራጣሪ ሁኔታዎች አሉበት:: ብዙ ኢኮኖሚስቶችን ለማወያየት ሞክሬአለሁ:: እና ብዙ አጠራጣሪ የሆኑ ሁኔታዎችን አይቻለሁ:: ዳታውን የሚሰበስበው ካድሬ ብቃት አለው ወይ? በወረዳ ደረጃ ዳታውን የሚያደራጁት ሰዎችስ ምን ያህል ይንቀሳቀሳሉ:: ከየትስ ነው ዳታው የሚሰበሰበው:: የተሰበሰበበት መንገድስ ትክክለኛ ነው ወይ? ለምሳሌ የእድገት ሁኔታ ከተነሳ ኢኮኖሚ ደጋግመው ሲገልፁ ይሰማል:: የሰውን ህይወት መለወጥ ያልቻለ ኢኮኖሚ አደገ አላደገ የሚለው ምናልባት የተወሰነው የህዝብ ክፍል ወደ ሰማይ ወቶ የሆናል:: ኢትዮጵያ ውስጥ በሚሊዬን የሚቆጠር ገንዘብ ሲሰረቅ ይስተዋላል:: ሙስና የሚባለው ነገር እኔ በጣም ያንገበግበኛል:: በጠቅላይ

ሚኒስትሩ ሪፖርት የጥቂት ነጋዴዎችን ስራ ለማጋለጥ የሞከረበት ሁኔታ ቢኖርም፡፡ የኢትዮጵያ መንግስት ሙሉ በሙሉ የተዘፈቀበት መስናን መከላከል አቅቶት ህዝብ ከዳር እስከ ዳር በሚጯጯህበት ሁኔታ ሙስናን ሳያነሳ ያለፈ ሪፖርት አጠያያቂ ነው፡፡

ጠቅላይ ሚንስትሩ ማንሳት ያልፈለጉት ወይም ያልቻሉት ከላይ የገለፅኳቸው እና ሌሎች ነጥቦችም አሉ፡፡ እነዚህን በጥሩ መንፈስ ተወያይቶ ችግሮቹን ለመፍታት በቻልን ነበር፡፡ ነገር ግን አልተቻለም፡፡ ምክንያቱም መንግስታቸውን የሚያጋልጥ ጉዳዩች እንዳይነሳ ስለሚፈልጉ፡፡

ደቂቃዎችን መዝነው ወይም ስንናገር እንዲቋረጥ የሚያደርጉት በአጭሩ ፖርላማው የክርክር መድረክ ሳይሆን የትምህርት ክፍል እየሆነ መቷል፡፡

***በአንድ ወቅት ጠ/ሚንስትሩ እርሶና ሌሎች የፖርላማ አባላት ጥያቄ ለፖርላማው ክብር ሲሉ መልስ እንደማይሰጡ ሲገልፁ ይስተዋላል፡፡ እንደ ህዝብ እንደራሲነትዎ ለዚህ ምን ምላሽ አለዎት?***

በሀገሪቱ ህግ መሰረት ስራ አስፈፃሚው የፖርላማ አባላት ለሚያነሱት ጥያቄዎች የግድ መልስ መስጠት አለበት፡፡ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ሲያስፈልግ ህጉን ይደፈጥጣሉ፡፡ እንጂ መመለስ የሚገባቸውን አልመለሱም፡፡ ማለት ይችላል፡፡ ምንም ይሁን ምን መመለስ ነበረባቸው፡፡ ከዚህ ይልቅ ግን የሚያስቀኝ ይህ አይደለም፡፡በፖርላማው ያለው የቃላት አጠቃቀም የዘለፋ ቃላት ናቸው መጨረሻ ላይ ጠቅላይ ሚንስትሩ ባቀረቡት ሪፖርት ላይ እኔ በጣም ተጠንቅቄ እናገር ነበር፡፡ ነገር ግን መሃል ላይ ከልጅነት እስከ ዕውቀት እጠቀምባት የነበረች አንድ አባባል ተናግሬ ነበር፡፡ «የኢትዮጵያ እድገት ላም አለኝ በሰማይ አይነት ነው» ብዬ ነበር፡፡ ይህ ደግሞ በእኛ ትውልድ እንደ ቀልድ የምትነገር ተረት ነበረች፡፡ ከዚህ ውጭ ምንም አይነት ሃይለ ቃልን አልተናገርኩም ነገር ግን ጠቅላይ ሚኒስትሩ የማይገባ እና ገደብ ያለፈ ንግግር ሲናገሩ የነበሩት ድንቁርና ነው ደንቆሮ ነው የሚሉ ንግግሮችን ይናገሩ ነበር፡፡ ከመሸታ ቤት ያገኘነው ዳታ አይደለም፡፡ IMFም የሚያውቀው ዳታ ነው እያሉ ይናገራሉ፡፡ ወቀሳም ካስፈለገ መወቀስ ያለባቸው እሳቸው ናቸው፡፡

***«በኢትዮጵያ የፖለቲካዊ ትግል ውስጥ የሰላማዊ ትግል አማራጮች ተዘግተዋል፡፡ ስለዚህ በጠብመንጃ አፈሙዝ ትግላችንን መቀጠል አለብን» የሚሉ አካላት ተፈጥረዋል፡፡ ይህንንስ ሁኔታ እንዴት የዩታል? ውጤቱስ?***

ሁለቱም የየራሳቸው ምክንያት አላቸው፡፡ «የሰላማዊ ትግል አቅጣጫ አብቅቷል» ብለው ተስፋ የቆረጡ ሰዎች ክርክሩ ያዋጣቸዋል፡፡ ኢህአዴግ ህግና ስርአትን አክብረው ሰላማዊ ትግልን ለሚከተሉ ሃይሎች መንገዶችን እያመቻቸ

አይደለም:: ብዙ ነገሮች ተስፋን የሚስቆርጥ እንጂ መንገድ እየከፈተ አይደለም:: ተቃዋሚዎች ህዝቡ ነፃና ፍተሃዊ ምርጫን አድርጐ የፈለገውን መምረጥ የመቻሉ ጉዳይ ተስፋ አይታይበትም:: ስለዚህ በሰላማዊ ትግል ተስፋ ቢቆረጥ አይገርመኝም:: እኛም እራሳችን በዚህ ዙሪያ ትልቅ ጥርጣሬ አለን:: በጠራራ ፀሃይ ያሉትን ተቋሞች ኢህአዴግን ተጠቁሞ ከመንገድ ለመጣ ሰው ፖርቲያችንን ያሰድድብናል የሚል አሳብ አንድ ቀንም በጭንቅላታችን መጥቶ አያውቅም:: ፖርቲያችን በተነጠቅንበት ጊዜ ቢያንስ ከ 120 ሺህ በላይ አባላቶች ነበሩን የከዱን ሰዎች ደግሞ 20-30 እንደሆኑ እርግጠኛ አይደለሁም:: የአንድ ፖርቲን ህልውናን ቁጥራቸው እጅግ ዝቅተኛ በሆኑ ሰዎች የ 120 ሺህ ህዝብ መብት ተገፏል:: በስራ አስፈፃሚ ማዕከላዊ ኮሚቴ በተለያዩ ደረጃ ያሉ አባላት እያሉ አባልነታቸውን እንኳን የምንጠራጠራቸው መንገደኞች ፖርቲያችንን ሲሰጥ ከዚህ በላይ ተስፋ የሚያስቆርጥ ነገር የለም:: ሌሎችም ድርጅቶች ለምሳሌ ቅንጅት ተመሳሳይ ችግር ገጥሞታል:: ስለዚህ ተስፋ መቁረጣቸው አያስገርመኝም::

የትኛው ትግል ያዋጣል የሚለው በዛሬይቱ አለም የጠበኛ ትግል ያዋጣል ብለው የሚታገሉ ሐይሎች አሉ:: ህጋዊና ሰላማዊ ትግል የተሻለ ውጤት ያመጣል ብለው የሚታገሉ አሉ:: አንዳንድ ጊዜም ሁለቱንም እያደባለቁ የሚጠቀሙ አሉ:: ትግሉን የሚወስነው የሃገሪትዋ የፖለቲካ መድረክ ነው:: የሚወስነው በግሌ የትኛውን ትመርጣለህ:: ኢህአዴግ በሩን ለሰላማዊ ትግል ዘግቷል::

ሰላማዊ ትግል በኢትዮጵያ አያዋጣም ብለው የሚከራከሩት ምክንያታቸው ይገባኛል:: በግልፅ ኢህአዴግ በሩን ዘግቷል:: ምርጫ እንኳን ከ97ቱ በብዙ እርምጃ ወደ ኃላ እንደሄደ ታያለህ::

***ከውጤት አንፃር ኢትዮጵያ ካላት የፖለቲካ ልምድ አጋጣሚዎች የትኛው የትግል ስልት አዋጪ ነው?***

ብዙውን ጊዜ እንደሚወራው በጠበኛ የመጣ ሐይል አምባገነን ይሆናል:: በምርጫ ሳጥን የመጣ ደግሞ የተሻለ ህዝባዊ እና ዲሞክራሲያዊ ስርዓት ይፈጥራል:: የሚለው ነገር እኔ ፖለቲካል ሳይንስን እስከማውቀው ድረስ እንደ ቀመር አልተቀመጠም:: ሁለቱም አካሄዶች ትጥቅ ትግልም ሰላማዊ ትግልም ውጤት ያመጣሉ:: በጠበኛ የመጣ ለውጥ ሁል ጊዜ አባገነናዊ ስርዓትን ይፈጥራል:: እያሉ አንዳንድ ሰዎች ሲናገሩ እሰማለሁ:: ከየት እንደመጣ አላውቅም የትኛው ይሻላል ብሎ መከራከር የተሻለ የሆናል:: በህጋዊ እና ሰላማዊ መንገድ መንዝ በሂደት ደረጃ የተሻለ ነው ብሎ መከራከር ይቻላል:: እኔም ብሆን ባለኝ አቋም አሁን ጫካ ለመግባት ፍላጐቱም የለኝም:: ህጋዊ እና ሰላማዊ

ትግልን በመቀጠል ረገድ እኔም ሆንኩ ድርጅቴ የምናምንበት መርህ ነው:: በአለም ደረጃ ባሉ ትግሎች እና ዴሞክራሲያዊ ስርአት ከመፍጠር አንፃር ሁለቱም ሊፈጠሩ ይችላሉ:: የአለም ተሞክሮ በጣም ሰፊ ነው:: ለምሳሌ በደቡብ አፍሪካ የፀረ አፖርታይድ ትግል የተካሄደው በሁለቱም የትግል ስልቶች ነው:: ደቡብ አፍሪካ ዛሬ የተሻለ ዴሞክራሲያዊ ስርአት የምታካሄድ አገር ናት:: ኪባኪ ስልጣን ላይ የወጣው በምርጫ ነው: ነገር ግን ስልጣን ላይ ሆኖ ይግባኝ ጠይቋል:: በምርጫ መምጣት የተሻለ ዴሞክራሰያዊ ስርአትን ይፈጥራል ማለት አከራካሪ ነው:: ናይጀሪያም ኦባሳንጆ በምርጫ ሳጥን ነው ስልጣን ላይ የወጣው:: ነገር ግን በምርጫ ስልጣን ላይ እንደወጣ ሰው አልነበረም ስራዎችን ሲሰራ የነበረው::

በኒኳራጉዋ ሳንዲስታ ስልጣን ላይ የወጣው በጠብመንጃ ነው:: ነገር ግን በምርጫ ከስልጣን ወርዶ እንደገና በምርጫ ስልጣን ላይ ወጥቷል:: ሳንዴስታዎች ይህንን ለውጥ ያመጡት በጠብመንጃ /በጉልበት/ ነው:: በአፍሪካ የተደረጉ የቀኝ ገዢዎችን ማስወገድ ትግል የተካሄደው ጠብመንጃም ተቀላቅለውበት ነው:: ጠበንጃ የግድ አምባገነናዊ ስርዓት ይፈጥራል:: በምርጫ ሳጥን ደግሞ ለውጥ ቢመጣ «አስተማማኝ የሆነ ዘላቂ የዲሞክራሲያዊ ስርአት ይፈጥራል» የሚለው በጥናት ደረጃ የተደገፈ አይደለም:: ሰዎች የየራሳቸውን ስሜት እና ፍላጎት ሊያንፀባርቁ ይችላሉ:: በእኔ ግን ሁለቱም ውጤት ለያመጡ ይችላሉ:: ዋናው መሰረታዊ ነገር ያንን የሚያካሂዱ ሃይሎች ምንድናቸው? ሁኔታቸው ምንድነው? ቅርፃቸው ምንድነው? አላማቸው ምንድነው? ምኞታቸው ምንድነው? ህልሞቻቸው ምንድናቸው? የሚሉትን መመለስ እንጂ በጠበንጃም ሆነ በሰላማዊ ትግል የማታገሉ ሀይሎች መሆናቸው አይደለም::

የትኛውን ስርዓት ይፈጥራል የሚለው ሕልሙ በጠበንጃ አፈሙዝ ስልጣን ላይ ወቶ አባገነን መሆን ከሆነ አንባገነን ይሆናል:: ህልሙ ዴሞክራሲያዊ ስርዓትን ለማስፈን ሲሞክር መንገድ ተዘግቶበት ህልሙን ለማሳካት ጠብመንጃ አንግቦ ጫካ የገባ ከሆነ እና ህዝባዊ አመኔታ እና ክብር ካለኝ ስልጣን ላይ እቆያለሁ:: ከሌለኝ ደግሞ ስልጣኑን እለቃለሁ የሚል ህልም ያለው ከሆነ ደግሞ በጠበንጃ አፈሙዝ ዴሞክራሲያዊ ስርአትን መፍጠር ይችላል:: ማለት ነው ጠብመንጃም በሃቅ ካነገቡት ዴሞክራሲያዊ ስርአት አያመጣም ማለት አይደለም:: አብዛኛው የአፍሪካ መሪዎች በምርጫ ሳጥን ስልጣን ላይ ወጥተው ስልጣን አንለቅም ብለው የሙጥኝ ያሉበት አጋጣሚዎች አሉ:: እንዲያውም በአፍሪካ እንደዚህ አይነቱ አጋጣሚ ነው የሚበዛው:: በዚህም ምክንያት ምርጫ የሚባለውን ወደ ጨዋታ የቀየሩ ብዙ አገሮች አሉ:: አንዱ መንገድ መንግስተ

ሰማያት ያስገባል አያስገባም የሚለው አያዋጣም ዋናው ነገር ግን የአገሪትዋ የፖለቲካ መድረክ ለየትኛው ያመቻል የሚለው ወሳኝ ነው፡፡ በሮች ካሉ የተወሰኑ ነገሮች ክፍት ከሆኑ ምንጊዜም ቢሆን ሰላማዊው ትግሉ ይሻላል፡፡ ሙሉ ለሙሉ ከተዘጉ ወይም ተስፋ ካስቆረጡ ሰው ስለፈለገ ወይም ስላልፈለገ ሳይሆን የግድ ወደ ጠበንጃ ትግሉ ያመራል፡፡ ለምሳሌ ምርጫ ሳጥን ላይ ሰው የሚደበደብ፣ የሚታሰር፣ የሚገደል ከሆነ እዚህ ሆኜ ከምሞት ሌላውን አማራጭ ልሞክር ብሎ ሁኔታው እራሱ ይፈጥረዋል፡፡ በኢትዮጵያ ህጋዊውን ትግል እኛ እንቀጥላለን ሌላው በዚህ ተስፋ የቆረጠው የሰላማዊ ትግሉ ሂደት እየጠበበ ነው፡፡ ተስፋ አስቆራጭ ነው ብለው የሚከራከሩ ሃይሎች እንደ ፖለቲካል ሳይንስ ባለሞያነቴ ክርክራቸው ይገባኛል፡፡ ነጥብም አለው፡፡

ኢህአዴግ ከሰላማዊ ትግል ይልቅ በጉልበት ፖለቲካ የሚያምን ይመስለኛል፡፡ «ምንም ያልያዘ፤ ዝም ብሎ የሚያወራን ሰው ተውት ምንም አያመጣም» እያለ ከታጠቁ ኃይሎች ጋር አስታርቁኝ ብሎ ሲማፀን እናያለን፡፡ ምክንያቱም የታጠቀ ሃይል ትንሽም ቢሆን ጉዳት አለው፡፡ ተቋማትን ያወድማል፣ ሰላምን ያቃውሳል፣ እራሱም የኃይል ፖለቲካን እያራመደ ስለሆነ የኃይል ፖለቲካውም ሊጎዳ ይችላል ብሎ የሚያምን ይመሰለኛል፡፡

***በኢትዮጵያ የፖለቲካ ትግል ለማድረግ ሲደራጁ ፖርቲዎች በዘር አልያም በህብረ ብሄራዊ ይዘት ከአገራዊ ፋይዳ አንፃር የቱ ያዋጣል?***

ህዝብ ችግሬን ይፈታል ብሎ ባመነበት መልኩ ሊደራጅ ይችላል፡፡ በዚህ መንገድ አትደራጁ ብሎ ማወጅ የከብዳል፡፡ ችግሮችን እፈታለሁ፡፡ ከመደራጀት የሆነ ጥቅም ይገኛል፡፡ ብሎ ካላመነ ሊደራጅ አይችልም፡፡ የህዝብ ችግር ካልያዘ በህዝቡ ተቀባይነት ከሌለ እና ህዝብ ካልተከተለ ማንኛውም ተደራጀሁ የሚለው አካል ቢኖር እንኳን ወጤት የለውም፡፡

በኢትዮጵያ ውስጥ የታሪክ ጣጣዎቻች አሉ ከነዚህ ታሪኮች የሚመነጩ ችግሮች አሉን፡፡ በአፄው ዘመንም ሆነ ከዛን በኃላ የኢትዮጵያ ህዝብ የኖረበት መንገድ የተወሰኑ የኢትዮጵያ ብሄሮች መብታቸው፣ ክብራቸው፣ ነፃነታቸው ተገፎ የነበረበት ሁኔታ ነበር፡፡ ስለዚህ እነዚህ እስኪፈቱ ድረስ በዛ መንገድ መታገሉ በዓለም ላይ የመጨረሻው ወንጀል ነው፡፡ ብሎ መኮነኑ ለእኔ የሚያዋጣ ጨዋታ አይመስለኝም፡፡ ሁላችንንም በዕኩልነት የሚያስተናግደን ፖለቲካዊ ሰርዓት እንዲፈጠሩ መታገል ግን የተሻለ አማራጭ ነው፡፡ በየትኛውም መንገድ የተደራጁ ሃይሎች አላማቸው የመበተን፣ አንዱ ሌላውን የመበተን ሳይሆን፣ አንዱ ሌላውን የመጉዳት አላማ ሳይሆን ተከባብረን የምንኖርበት ኢትዮጵያን ሁላችንንም በእኩልነት የሚያስተናግድ ፖለቲካዊ ስርዓትን መፍጠር አለብን፡፡

ልዩነቶችን አስታርቀን የታሪክ ቁርሾዎችን፣ ችግሮችን የተወሰነውን ለታሪክ በመተው የተወሰነውን ደግሞ ለዛሬው ትውልድ በሚሆነው መለኩ እየፈቱ መንቀሳቀስ ያባት ነው::

በብሄር የሚደራጁ ሃይሎች ጉልበታቸውን እውቀታቸውን ድርጅታቸውን ፍላጎታቸውን ሁሉ ጥንት የነበረውን የታሪክ እከኮች እና ቁስሎችን እያከኩ የኢትዮጵያ ህዝብ አብሮ ሰፊ አገራዊ ራዕይ ይዞ የተሻለች እና የበለፀገች ኢትዮጵያን ለመፍጠር ከመታገል ይልቅ ያንን እያከኩ ሰፊ አገራዊ ጉዳዮች ላይ አቋም እንዳይዙ እንቅፋት በመሆን መልኩ ከተንቀሳቀሱ ችግር የመፍታት ሳይሆን የበለጠ ችግር ወደ መፍጠሩ ነው የሚሄዱት:: በአብዛኛው መመዘን ያለባቸው ለምን አላማ ይታገላሉ ነው:: ተከብሮ ለመኖር ሁሉንም በእኩልነት የሚያስተናግድ ስርአት እንዲፈጠር ነው የሚታገሉት ወይስ ለሌላ ጠባብ አላማ ነው የሚታገሉት የሚለውን መለየት ያስፈልጋል:: አለበለዚያ ግን በዚህ መለኩ መደራጀት ጥሩነው አይደለም እያሉ ከድምዳሜ መድረስ ጥሩ አይመስለኝም::

### *በኢትዮጵያ ውስጥ በብሄር ፌደራሊዝም እንከተላለን መባሉስ እንዴት ይመለከቱታል?*

እኛ ሀገር የትኛውን አይነት አሰራር እንደምንከተል ግራ ይገባኛል:: ምክንያቱም የሚባለው ስራ ላይ እየዋለ አይደለም:: የብሄር መብቶች ኢትዮጵያ ውስጥ እየተከበሩ አይደለም:: ለምሳሌ የህገ መንግስቱ አንቀፅ 39 ኢህአዴግ ሰልጣን ላይ እስካለ ድረስ ስራ ላይ አይውልም:: ሌሎችም መብቶችም ቢሆኑ ለጠየቁ ህዝቦች እየተሰጠ አይደለም::

አሁን ኢትዮጵያ ውስጥ ያለው ፌደራሊዝም ስለመሆኑም እጠራጠራለሁ:: በአብዛኛው በወረቀት ላይ የተፃፈ ፌደራሊዝም እንጂ በጋሀድ እውነታ ግን የማይተረጎም ፌደራሊዝም እያየሁ ነው:: አለ ብለን ካልን እንኳን ገዢው ፖርቲ ለከፋፍለህ ግዛ ስትራቴጂ የሚጠቀምበት እንጂ ህዝቦች ተከባብረው በዕኩልነት ለጋራ ሀገር የየራሳቸውን አዋተው የሚኖሩበት ስርአት እየፈጠረ አይደለም:: ፌደራሊዝም ያለ ዴሞክራሲያዊ መሰረት ሊኖር አይችልም:: የእኛ አገር የዴሞክራሲያዊ ሁኔታ ደግሞ የሳሳ ወይም የጠበበ ነው:: ያለ ዴሞክራሲ መሰረት ደግሞ ፌደራሊዝም ብለን ሰም ስለሰጠነው ብቻ ፌደራሊዝም አይሆንም:: የህዝቦችን መብትን፣ የአካባቢ መብቶችን (እያንዳንዱ ብሄር የራሱን አካባቢ በፈለገበት መንገድና ሁኔታ እያስተዳደረ መሪዎችን በፈለገው መንገድ እየመረጠ ሃብትና ንብረቱን በራሱ መንገድ እንዲጠቀም) ማክበር ባልተቻለበት ሁኔታ ገዢው ፖርቲ ለራሱ አላማ የፈጠረው ካለሆነ በቀር ፌደራሊዝም በእውነተኛ ኢትዮጵያ ውሰጥ አለ ለማለት ያስችግራል ምናልባት እኛ የማናውቃት ሌላ ኢትዮጵያ ከሌለች በቀር::

***የቅንጅት አመራሮች ሲታሰሩ ዶ/ር ብረሃኑ ከእርሶ ጋር የመጨረሻዋን የስልክ ውይይት እያደረጉ ነበር ስለምን ነበር የምታወሩት?***

በእርግጠኝነት ስለምን እንዳወራን አሁን ትዝ አይለኝም:: ስልክ መደዋወላችን ግን ትዝ ይለኛል:: የማስታውሰው ነገር ቢኖር «መረራ በል እያሰሩኝ ነው» የሚለው ትዝ ይለኛል:: ጊዜው ስለራቀ ስለምን እንዳወራን ለምን እንደተደዋወልን ትዝ አይለኝም:: «በል መራራ ሊያስሩኝ ነው» የምትለዋ ንግግር ግን አልረሳትም:: ከዶ/ር ብርሀኑ ጋር ከዛች የስልክ ልውውጥ ጀምሮ እስከ ዛሬ አለተገናኘንም::

***የቅንጅት አመራሮች መታሰራቸውን ሲሰሙ ምን ተሰማዎት?***

ምን ግልፅ ነበር እኮ:: የተጠበቀ ነበር:: የመንግስት መሪዎች ጠቅላይ ሚኒስተር መለስ ዜናዊን ጨምሮ እንዲህ ካላደረጋችሁ እናስራችኃለን ብለው ሲናገሩ ነበር:: በዲኘሎማቲክ ኮሚኒቲውም በኩልም ቢሆን እንዲህ አይነቱ መልዕክት ይተላለፍ ነበር:: ከዚህ በኃላም ደግሞ ድርድር አቋርጠን ስንወጣ በግልፅ ቋንቋ አንዳንዴም በተለያዩ መንገዶች እነማን እንደሚታሰሩ ይነገርም ነበር:: ከዚህም ባለፈ የሰዎች ሊስተም .... ነበር:: ይመስለኛል ህብረቱም አካባቢ የተወሰኑ ነገሮች ነበሩ:: ምናልባት ፖርላማ በመግባታችን የህብረቱን መሪዎች ከመታሰር ያዳነ ይመስላል:: የመታሰሩ ነገር ምንም የተደበቀ አልነበረም::

***ኢህአዴግን በመፀሀፍ ላይ ወታደራዊ በህሪ ያለው መንግስት (Quasi - Military) ብለው ፅፈዋል ምክንያትዎት ምንድነው?***

ዋነኛ ምክንያቴ ኢህአዴግ በዕዝ ሰንሰለት ስለሚንቀሳቀስ ነው:: ፖርቲያቸው እና የሚያንቀሳቅሳቸው የመንግስት ተቋማት በዕዝ ሰንሰለት ነው የሚንቀሳቀሱት:: ትዕዛዝ ከላይ ትሰጣለህ እስከታች ድረስ ይህ ትዕዛዝ ተፈፃሚ ይሆናል:: ግልፅነት የሚጎላቸው እንደ ወታደራዊ ተቋማት ነገሮች ሁሉ ምስጢር ተደርገው የሚያዩበት አሰራሮች ይከተላል:: ውሳኔዎች ሳይቀሩ በሚስጥር ተይዘው ነገሮቹ ሁሉ የወታደር ነው ስህተት ተሰራ እንኳን ተብለው ለመጠየቅ የአሰራር ግልፅነት ባለመኖሩ ማን የት ጋር እንዳጠፋ አታውቅም::